# ጀግኖቹ የት ሄዱ

ሞትን ሙት አድርገው ህያው የነበሩ
ለፍትህ ለአርነት ቀንዲሉን ያበሩ
እንዴት ከቀያቸው ጠፉ ከምድሩ

ለጅግና ሞት ሽሚያ ማንንም ሳይፈሩ
እንዴት ተረጋግጠ ይጥፋ መቃብሩ

ሲሞሉ ሲፈሱ ድርጭቶች ሲከብሩ
የጀግኖቹን ወንበር ለመያዝ ሲበሩ
መስሎ ማደር ዘይቤን ተላብሰው የሚኖሩ
በህሊና ጸጸት ደንዝዘው ሳያፍሩ
እስስትን አስንቀው አገር የሚመሩ

ለአፈር የታዘዘው አይኔ ተመልክቶ
ለፍትህ ለአርነት መታገል ተረስቶ
ለሆድ ማደር ዘይቤ በእግር ተተክቶ
አገሩን ሞልቶታል የእኔነት ቀረርቶ

ፍትህን ለማንገስ ስርዓትን ለውጠው
በጠበል ደማቸው አገሪቱን እረጭተው
ተሸከመው መስቀል በእርቃነ ስጋቸው
ቀንዲሉን ያበሩ በአጥንት በደማቸው
ዛሬ ወዴት ሄዱ? ጨለማ ዋ! ጣቸው

ይሆን ወይ ልውጥ ዘር
በጣጥሶ የጣለ የማተቡን ክር
ከሆዱ ያልራቀ የሚያስበው ነገር
በጀግኖቹ አገር ተተክቶ የሚኖር

የጀግኖቹ አጥንት ሲለቀም ከጉድጓድ
ንስሐ አልባ ገዳይ ንዴቱ ሲል አልበርድ
አንዴ በህይወታቸው አንዴ በሞታቸው
በለጋ ዕድሜአቸው በለጋ ሞታቸው
አንዴ በስጋቸው በደም አጥንታቸው
ላደረሱት በደል ቅር ሳይላቸው
የትንኝ ደም ያህል ጸጸት ሳይገባቸው
ዕልባት በሌለው ድንፋታ ዛቻቸው
በየፍርድ ቤቱ ሲነሳ ስማቸው
በሆዳም ከርሳሞች ሲቀለድባቸው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ባለቤት የሌለው አዛኝ ተቆርቋሪ
ጎጥና መንደሩ ተከቦ በፈሪ
ድብልቅ አንደበት ያልሆነውን አውሪ
በፍርሐት ጽልማሞት ሁሌ ተሽከርካሪ

“ወንድሙ ሲገደል ወንዱሙ ካልከፋው
አምጡና አሽትቱት ደሙ እንዲከረፋው”

ተብሎ ሲነገር በቃል ሲተገበር
የጀግና ልጅ ጀግና ሲሆን እንዳልነበር

የደሙ መከርፋት ሽቶ እየሆነበት
ቁልል ነዶው አጥንት ከሌለው ልዩነት
ከአህያ ከጅቡ ለውጡን ካላየበት

በደም የጨቀየ ጥይት የበሳሳው
በዘመናት ብዛት ወይቦ የሚታየው
ቁጣና ወኔውን ደጋግሞ ካልጫረው
ምኑን እናሽተው ምኑን እናሳየው
ምኑን ብናሰማው ያስነሳዋል ወኔው

የሰው መገለጫ የቁጭት ቋጠሮ
አጥንትና ደሙ ጨርቁ ተደምሮ
ዕልህና ቁጣን ካልፈጠረ ጭሮ
ምኑን እናሽተው እንዲገዛ አእምሮ
ለፍትህ ነጻነት እንዲዋጋ አምሮ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com